## ህብረተሰቡ... ከገፅ 4 የዞረ

አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ በግልፅ የሚታየው ዋልታ ረገጥ ኃይሎች ሲጨፍሩ፣ ከ90 በመቶ በላይ የሆነው አብዛኛው (ብዙሃኑ) ህዝብ (the Silent Majority) ዝም ብሎ ተመልካች ሆኗል ይህ አሁኑኑ መለወጥ አለበት፡፡ ሜዳውንም፣ወሬውንም መሳሪያውንም፣ ቃላቱንም ለፅንፈኞች ትቶ ሊላው ፀጥ ብሎ እየተመለከተ መሆኑ አደጋ ሊያመጣ ይችላል፡፡ ብዙሃኑ ዝም ያለው ህዝብ ራሱንም ሀገሪቱንም ለማዳን ዛሬውኑ መንቀሳቀስ መጀመር አለበት፡፡ ንዑስ ከበርቴው (የእኔ አይነቱ) አንድ ቤት ካለው ሁለተኛ ቤት ለመስራት፣ አንድ መኪና ካለው ሌላ መኪናውን ለመጨመር የተጨነቀ (obsessed) የሆነ ይመስለኛል፡፡ ግጭትና ጦርነት ከመጣ ቤትም፣ ልጆችም፣ ቤተሰብም፣ መኪናም፣ ገንዘብም ዱቄት ይሆናል፣ ልጆችም ይጠፋሉ፡፡

መፍትሔው ህዝቡ ራሱን ማደራጀት አለበት፡፡ በሀገር ደረጃ፣ በከተማ፣ በገጠርም ራሱን ከፅንፈኛ ኃይሎች ለመከላከል መደራጀት አለበት፡

**አዲስ ልሳን፡- በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል የወረደው ሰላም በአፍሪካ ቀንድ ላይ ምን እንድምታ ይኖረዋል?**

**ፕ/ር ተስፋዬ፡-** በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል የወረደው ሰላም ትልቅ ክስተት ነው። እንደ ሚታወቀው ለ20 ዓመታት የዘለቀውን መፋጠጥ ፈረንጆች እንደሚሉት 'No War, No Peace' ማለት ጦርነትም ሆነ ሰላም የሌለበትን ሁኔታ የለወጠ ክስተት ነው፡፡ በምድር ላይ እንደዚህ ዓይነት መጥፎ ነገር የለም፡፡ 20 ዓመት የተቃጠለ ጊዜ ማለት ነው፡፡ ሁለቱም ሀገራት ያጠፉትን ሀብት ለልማት ቢጠቀሙበት ኢኮኖሚያቸውን ትልቅ ደረጃ ማድረስ ይችሉ ነበር፡፡

እንደሚታወቀው የዛሬ 2 ዓመት ገደማ ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተጠበቀ ሪፎርም ተካሄደ፡፡ ዶክተር አብይ አህመድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ፡፡ ይህንን ለውጥ ተከትሎ በአንዳንድ የአካባቢው ሀገሮች ሸምጋይነት ወደ ሰላማዊ መንገድ እንዲሄድ ተደርጓል፡፡ እዚህ ላይ ሳውዲ አረቢያና የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ትልቅ ሚና የተጫወቱ ይመስለኛል፡፡ ይህ የሰላም ስምምነት ለኢትዮጵያና ኤርትራ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ ቀንድ ቀጣና፣ ከዛም አልፎ ለመካከለኛው ምስራቅ ትልቅ እንድምታ ይኖረዋል፡፡ በአካባቢው ሰላምና መረጋጋትን ለዘለቄታው ሊያሰፍን ይችላል። ሰላም ካለ ደግሞ የኢኮኖሚ እድገት ይኖራል፡፡ ሰላምና መረጋጋት ካለ የፖለቲካ መረጋጋት እንዲሁ ሊፈጠር ይችላል፡፡

ኢትዮጵያ ከ100 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ያላት ትልቅ ሀገር ሆና የባህር በር የሌላት ሀገር ሆናለች። ከኤርትራ ጋር ሰላም መፍጠሩ ኢትዮጵያን አማራጭ የወደብ አቅርቦት በተሻለ ዋጋ ማግኘት የምትችልበት መንገድ ይከፍታል፡፡ የኢትዮጵያና ኤርትራ ህዝብ አንድ ህዝብ ነው፡፡ ለብዙ ዓመታት አብሮ የኖረ፣ የተዋለደ ህዝብ ነው፡፡ ሰላም ሲኖር የህዝቦችን ነፃ ዝውውር ይፈጥራል፡፡ ሰዎች እን ደፈለጉ መዘዋወር፣ ሸቀጥና ካፒታል እንደፈለጉ ማንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡ ስምምነቱ ለሁለቱም ሀገራት ጠቃሚ ነው፡፡

**አዲስ ልሳን፡- ስምምነቱ እንደተጀመረው ወደፊት ተራምዷል ብለው ያስባሉ?**

**ፕ/ር ተስፋዬ፡-** አጀማመሩ ጥሩ ስለነበር እኔ ከዚህ በላይ ነበር የጠበቅኩት፡፡ ነገሮች በፍጥነት ሄደው፣ ድንበሩ ተከፍቶ፣ ነፃ የህዝብ እንቅስቃሴ በአየር ብቻ ሳይሆን በየብስ ትራንስፖርት ይኖራል የሚል ግምት ነበረኝ፡፡ አሁን አንዳንድ ነገሮች ግልፅ አይደሉም፡፡ ለምን በኤርትራ በኩል ድንበሩን ከፍተው እንደገና እንደዘጉት በይፋ የተገለፀ ነገር የለም፡፡ ምክንያት ይኖራቸዋል፡፡

በኢትዮጵያ በኩልም ለምን ሁኔታዎች በተ ጀመረው ፍጥነት አልሄዱም የሚለው እስከአሁን በይፋ የወጣ መረጃ ስለሌለ ምክንያቱን አናውቀውም።

**አዲስ ልሳን፡- የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ሀገራት በኢኮኖሚው የሚተሳሰሩበትና ወደ ኮንፌዴራላዊ ቀጣና ማደግ የሚችሉበት ዕድል ምን ያህል ነው?**

**ፕ/ር ተስፋዬ፡-** ይኼ የቆየ ግን እስከአሁን መልስ ያላገኘ ጥያቄ ነው፡፡ ኮንፌዴሬሽን እንደ አንድ ትልቅ አማራጭ አድርገው የፃፉ ምሁራን አሉ። አንዱ በዚህ ላይ ብዙ ፅሁፍ ያቀረቡት ፕሮፌሰር ተስፋጽዮን መድሃኔ ይባላሉ፡፡ ኤርትራዊ ናቸው። የሚያዳምጥ ጠፍቶ ነው እንጂ ብዙ ፅፈዋል። የእርስ በርስ እንዲሁም የውክልና ጦርነት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ አለ፡፡ በሀገሮች መካከል አለመግባባት አለ። ባለፈው ኤርትራ ከኢትዮጵያ፣ ጅቡቲና ሌሎችም ጋር ችግር ነበረባት፡፡ በዚህ ምክንያት ኮንፌዴሬሽን የሚታሰብ ነገር አልነበረም፡፡ ኮንፌዴሬሽንን ተግባራዊ ለማድረግ በሁሉም ዘንድ ሰላምና መተሳሰብ መኖር አለበት፡፡ ሁሉም ይጠቀምናል ብለው ማመን አለባቸው፡፡ ለምሳሌ የአውሮፓ ህብረት ሀገራት አንድ ከመሆን አልፈው አንድ ገንዘብ ዩሮን ነው የሚጠቀሙት፡፡ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ኮንፌዴሬሽን የማይፈፀምበት ምክንያት የለም፡፡ ይኼን የምልበት ምክንያት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የባህል ትስስር አለ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ትስስርም ያለበት ቀጣና ነው። እንዲሁም ችግሮችን በተለያየ ደረጃ ይካፈላሉ፡፡ ለምሳሌ ድርቅ ከመጣ ሁሉም ጋ ነው የሚመጣው፡፡ ረሃብም እንደዚያው፡፡ የአካባቢ መራቆት፣ ድህነት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት ካለ ሁሉም ላይ ተፅዕኖ ስለሚኖረው የጋራ ጥረት አስፈላጊ ነው፡፡ የጋራ ጥረት አስፈላጊ ከሆነ የኮንፌዴሬሽን አስፈላጊነትን ያመጣል፡፡ በኮንፌዴሬሽን መተሳሰር የጋራ ጥረት፣ የጋራ መፍትሔ ማምጣት ይቻላል፡፡

በአሁኑ ወቅት ኮንፌዴሬሽን በአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ለማምጣት ችግሮች ይታያሉ፡፡ በአፍሪካ ቀንድ በተለይም ኢትዮጵያ ጎጠኝነት፣ የሰፈር አስተሳሰብ እና የሃይማኖት አክራሪነት ይታያል። ይታያል፡፡ ልክ የአውሮፓ ህብረት እንዳደረገው ወደ ኮንፌዴሬሽን ለመሄድ ጭንቅላትን ሰፋ ማድረግ ይጠበቅብናል። አንተ ኢትዮጵያዊ ሆነህ ስለሀገርህ ብቻ አይደለም መጨነቅ ያለብህ፡፡ ስለአፍሪካ ቀንድ ከዚያም ባለፈ ከአፍሪካ ቀጥሎ ስለዓለም መጨነቅ አለብህ፡፡ በሚዲያ ጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ጉዳት አደረሰ ሲባል በሰብአዊነት ታዝናለህ፡፡ በአፍሪካ ቀንድ እና በተለይም ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቁ ችግር በጭንቅላት ላይ ብዙ አልተሰራም፡፡ ፈረንጆች 'ኮስሞፖሊታን' የሆነ አስተሳሰብ፣ ማለት ከጎጥህ ወጥተህ ስለዓለም፣ ስለአፍሪካ፣ ስለ ሰው ልጅ የምታስብበት ግንዛቤ መፈጠር አለበት፡፡

**አዲስ ልሳን፡- የህዳሴውን ግድብ የውሃ አሞላልና አለቃቀቅን በሚመለከት ሶስቱ የተፋሰሱ ሀገራት እያደረጉ ባሉት ድርድር ግብፅ በተደጋጋሚ እን ደሚታየው ላለመስማማት የምትስማ ማው እንዲሁም ችግሩ ከቴክኒካዊ መፍትሔ ይልቅ በዲፕሎማሲ እንዲያ ልቅ የምትፈልገው ለምንድን ነው?**

**ፕ/ር ተስፋዬ፡-** ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ ግብፆች ቴክኒካል ጉዳይ ከመጣ እንደማያዋጣቸው ያው ቂታል፡፡ ስለዚህ ቢቻል በዲፕሎማሲ ካልሆነ በማስፈራራት እነሱ በሚፈልጉት መንገድ የግድቡ ውሃ አሞላልና አለቃቀቅ እንዲካሄድ ይፈልጋሉ። አሁን በቅርቡ የውሃው ሙሌት ከ12 እስከ 20 ዓመት እንዲሆን ብለው ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ ይኼ በጣም የሚያሳዝንም የሚያስቅም ነው፡፡ ከ12 እስከ 20 ዓመት ግድቡ ይሞላ ማለት ግድቡ ከጥቅም ውጭ ይሆን እንደ ማለት ነው፡፡ አንድ መኪና አቅመኸው ከአንድ ዓመት በኋላ ብትመጣ ምንም አገልግሎት ስላልሰጠ ዝገ ብዙ ነገሩ ተበላሽቶ ታገኘዋለህ፡፡በዚህም በዚያም የውሃው ማከማቻ ከሞላ በኋላ የአባይ ወንዝ የተፈጥሮ ፍሰቱን ጠብቆ እንዲሄድ መደረግ አለበት ነው የሚሉት፡፡ ኢኤአ በ1959 ግብፅና ሱዳን "የናይል ውሃ ስምምነት ብለው የተፈራረሙት ኢትዮጵያን ሳያሳትፍ ሁለቱ ሀገራት ብቻ ተቀምጠው ግብፅ 55 ነጥብ 5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ፣ የተቀረውን 18 ነጥብ 5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ደግሞ ሱዳን እንድትወስድ የሚለው መከበር አለበት ነው የሚሉት፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ያኔ ስምምነቱ ኢትዮጵያን አይመለከትም ብሎ በጉንስ ነገሩ ዘመን መግለጫ አውጥቷል፡፡ ማስፈራራቱም ሆነ ውሃ በዚህ መጠን መለቀቅ አለበት የሚሉት እነዚህ የግብፅ ሀሳቦች የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ጥቅም የሚጻረሩ ናቸው። እንደሚታወቀው የናይል 85 በመቶ ውሃ ከኢትዮጵያ ነው የሚሄደው፡፡ ኢትዮጵያ በአባይ ውሃ ሙሉ በሙሉ የመጠቀም መብት አላት። እርግጥ ነው፣ ሙሉ በሙሉ የመጠቀም መብት አለህ ማለት ሌላው ሀገር እንዳይጠቀም ማድረግ አለብህ ማለት አይደለም፡፡ ለግብፅ ሕዝብም መታሰብ አለበት፡፡ ይህም ሆኖ ኢትዮጵያ ግብፅ አሁን በምታቀርበው ቅድመ ሁኔታ በምንም ተአምር መስማማት የለባትም፡፡ በኢትዮጵያ በኩል ውሃ ማከማቸቱ በመጪው ክረምት ይጀምራል፡፡ ከ13 የውሃ ማመንጫ ተርባይኖች ሁለቱ በታህሳስ 2013 ዓ.ም ኃይል ማመንጨት ይጀምራሉ ተብሎ ይጠበቃል። እነዚህ ስራዎች በፕሮግራሙ መሰረት መካሄድ አለባቸው ነው የምለው፡፡



**አዲስ ልሳን፡- በድርድሩ አሜሪካ በታዛቢነት የተጋበዘችው ለምንና በምን ሁኔታ ነው?**

**ፕ/ር ተስፋዬ፡-** አሜሪካ እንድታደራድራቸው የተማፀኑት የግብፁ ፕሬዝዳንት አል ሲሲ ናቸው። በተለያዩ ታሪካዊ ምክንያቶች ግብፅና አሜሪካ ከካምፕ ዴቪድ ስምምነት ጊዜ ጀምሮ ጠበቅ ያለ ግንኙነት ነው ያላቸው፡፡ እንደሚታወቀው በዓለም ላይ ከአሜሪካ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ እርዳታ የምታገኘው አንደኛ እስራኤል ስትሆን፣ ሁለተኛዋ ግብፅ ናት፡፡ ይመስለኛል በግብፆች እሳቤ ኢትዮጵያ ከአሜሪካ ብዙ እርዳታ ስለምታገኝ ተፅዕኖ ልታደርግ ትችላለች ወይንም አሜሪካንን ሲያዩ የኢትዮጵያ ተደራዳሪዎች ሊፈሩ ይችላሉ ብለው ገምተው ሊሆን ይችላል ካይሮ፣ ካርቱምና አዲስ አበባ እያልን ከምንመላለስ በኃያሏ ሀገር አሜሪካ የዓለም ባንክ እና የአሜሪካ የገንዘብ ሚኒስትር ባሉበት ብንደራደር የተጨበጠ ውጤት ያመጣል ብለው ወደ አሜሪካ የወሰዱት ይመስለኛል፡፡

**አዲስ ልሳን፡- በናይል ተፋሰስ ሀገራት አሁንና ወደፊት ሊፈጠሩ የሚችሉ የውሃ ፖለቲካ ግጭቶችን ለማስቀረት ምን መሰራት አለበት?**

**ፕ/ር ተስፋዬ፡-** ይህንን ለማድረግ ሁሉም አሸናፊ የሚሆኑበትን ነገር (Win-Win solution) መፈለግ ያስፈልጋል፡፡ አንዱ ወገን የራሱን ጥቅም በማስከበር ሌላው እንዲጎዳ (win -lose solution) ከሞከረ አንዱ ተሸናፊ ሌላው አሸናፊ አይሆንም። ምክንያቱ በመጨረሻ ውጤቱ ሁሉም ተሸናፊ የሚሆኑበት (lose- lose) ይሆናል፡፡

ናይል የጋራ ሀብት ነው፡፡ ድንበር አቋራጭ ወንዝ ነው፡፡ የጋራ ሀብትና ድንበር አቋራጭ ወንዝ ላይ ልክ እንደ ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ለምሳሌ ሴኔጋል፣ ኮሎራዶና ሚኮንግ ወንዞች ሁሉም ተነጋግረው ተስማምተው አሸናፊ የሚሆኑበትን መንገድ መፈለግ አለባቸው፡፡ እኔ ነኝ የተሻለ አቅም ያለኝ፣ ድምፅን በድምፅ የመሻር መብት አለኝ፣ በታሪክ ተጠቃሚ ነበርኩ፣ እናንተን አላውቃችሁም ከተባለ ችግር ይፈጠራል፡፡ አሁን በአባይ ላይ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ በሚያሳዝን ሁኔታ ይኼ ነው፡፡

መፍትሔ ከተፈለገ ከኢትዮጵያ ይልቅ ብዙ ነገር በግብፅ ሜዳ ላይ ነው ያለው፡፡ ግብፅ አጨቃጫቂ የሆኑትን ከቅኝ ግዛት በፊትና በኋላ የነበሩ የናይል ወንዝ ስምምነቶችን እስከአሁን ልክ ናቸው ተግባራዊ መሆን አለባቸው የሚል ግትር አቋሟን ሙሉ በሙሉ መለወጥ አለባት። መፍትሔው የዛሬ 10 ዓመት አካባቢ የተዘጋጀ የናይል ተፋሰስ ትብብር ማዕቀፍ (Nile Basin Coperative framework) ባጭሩ CFA ሰነድን መፈረም ነው፡፡ ስድስት ሀገራት ማለትም ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ዩጋንዳ፣ ብሩንዲ እና ሩዋንዳ ፈርመዋል፡፡ ከእነዚህ ሀገራት ሶስቱ ኢትዮጵያን ጨምሮ ለፓርላማቸው አቅርበው አፀድቀውታል፡፡ ግብጽና ሱዳን እስከዛሬ ባለመፈረማቸው ሰነዱ ፀድቆ ስራ ላይ ሊውል አልቻለም፡፡ በጥሞናና በሰከነ መንገድ ካሰቡበት ሰነዱ ለሱዳንም ሆነ ለግብፅ በጣም ጠቃሚ የሆነ ስምምነት ነው፡፡ ያለነው 21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነው፡፡ የህዝብ ቁጥር እየጨመረ መጥቷል፡፡ አዳዲስ ችግሮች በየጊዜው እየተፈጠሩ ነው፡፡ ሁኔታዎች እንዲህ ባሉበት ሁኔታ የቆዩ፣ ሁሉም ያልተስማሙበትን ስምምነቶች ተቀበሉ ማለት አያዛልቅም፡፡

ግብፅ ከሁሉም ከናይል ተፋሰስ ሀገራት በአንፃራዊ መልኩ ያደገች ነች፡፡ አቅሙም ሀብቱም ያላት ሀገር ነች፡፡ ናይል ረጅም ወንዝ ቢሆንም ትንሽ ውሃ ይዞ የሚሄድ በመሆኑ እሱ ላይ ብቻ ከማተኮርና ከመፋጠጥ ሌሎች የውሃ ምንጮችን መጠቀም ትችላለች፡፡ እስራኤሎች የታወቁበትን የጠብታ መስኖ መጠቀም ብዙ ውሃ ለመቆጠብ ይረዳል፡፡ አጠገባቸው ሜዲትራኒያን ባህር፣ ቀይ ባህር አለ፡፡ ውሃ ከዚህ ጨለፍ አድርጎ ጨው አልባ በማድረግ መጠቀም ይችላሉ፡፡ ውሃ እንደገና አጣርቶ የመጠቀም አቅሙም አላቸው፡፡ እንዲሁም የከርሰ ምድር ውሃ ብዙ ስላላቸው እነዚህን አጎልብተው ቢጠቀሙ ለእነሱም ለሌሎችም የተፋሰስ ሀገሮች የሚበጅ መፍትሔ ይመስለኛል፡፡

**አዲስ ልሳን፡- አፍሪካዊያን ችግሮቻቸውን በውስጥ አደረጃጀታቸው የመ ፍታት ልምዳቸው ምን ያህል እየጎለበተ መጥቷል?**

**ፕ/ር ተስፋዬ፡-** የአፍሪካ ህብረት የአፍሪካን ችግሮች በአፍሪካዊያን መፍትሔ መስጠት የሚል ጥሩ መፈክር አንግቧል፡፡ ይህ ነገር መጎልበት አለበት፡፡ ለምሳሌ የናይልን ያልተፈቱ ችግሮች ይዞ አትላንቲክ አቋርጦ ዋሽንግተን ዲሲ ድረስ ይዞ መሄድ ለእኔ አይታየኝም፡፡ የናይል ወንዝ ያለው እዚህ ነው፡፡ ለምን እዚያ እንሄዳለን?፡፡ ይኼ መፍትሄ ማግኘት ያለበት ወንዙ ከሚፈስባቸው ሀገሮች ጋር በመነጋገር ነው፡፡ ዋሽንግተን ዲሲ መሄድ የአፍሪካን ችግሮች በአፍሪካዊያን መፍታት ከሚለው መርህ በተፃራሪ የቆመ ነው፡፡ ለአፍሪካ ህብረትም የሚያሳፍር ነው። ለምሳሌ አሁንም እልባት ያላገኘው የናይል ድርድር በዚህ ወር መፍትሔ ካላገኘ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ ደቡብ አፍሪካ ለጉብኝት ሄደው ፕሬዝዳንት ራማ ፎዛን ቃል ባስገቡት መሰረት ደቡብ አፍሪካ እንድትሸመግል ማድረጉ የአፍሪካ ሕብረትን መፈክር ተግባራዊ ማድረጊያ ምሳሌ ይሆናል፡፡

**አዲስ ልሳን፡- ውድ ጊዜዎን ሰውተው ስለሰጡን ሰፋ ያለ አስተያየት እናመ ሰግናለን**

**ፕ/ር ተስፋዬ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡